Qa.A.R.Maqaadin Gaddih Daddosih Biiro
**የአፋር ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ**
AFAR MINES RESOURCE DEVELOPMENT BUREAU

:ixxima:. malgal da 4/77
ቁጥር:.
: Ayro 21/09/2015
:ቀን:.

**ለሚመለከተው ሁሉ**

**ጉዳዩ፦ <u>የድጋፍ ደብዳቤ ስለመስጠት</u>፤**

ሀገራችን ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ የተፈጥሮ ሀብቶች የበለፀገች በመሆኗ በተለይም የአፋር ብሔራዊ ክልል በማዕድን ሀብት የሚታወቅ በመሆኑ መንግሥት የማዕድን ዘርፉን በልማት ለማሳደግ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የአፋር ቤንቶናይት ሚኒራል ማይኒንግና ፕሮዳክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር በቤንቶናይት ማምረት ሥራ ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፈሰስ ፋብሪካ ገንብቶ ለብዙ ወጣቶች የሥራ ዕድል የፈጠረ ድርጅት ነው፡፡

እንደሚታወቀው ቤንቶናይት በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች በተለይም በክልላችን በስፋት የሚገኝ ሆኖ ሳለ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እየተከፈለበት ከውጭ ሀገራት እየገባ ይገኛል፡፡ አፋር ቤንቶናይት በዚህ ምክንያት እየወጣ ያለውን የውጭ ምንዛሬ በሀገር ውስጥ እንዲቀር ከማስቻሉም በላይ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ የተረፈውን ምርት ወደ ውጭ ሀገራት በመላክ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ በመሆን እየሠራ ይገኛል፡፡

ስለሆነም እንደዚህ ያሉ ሀገር በቀል አምራች ድርጅቶችን ማገዝና ማበረታታት ተገቢ በመሆኑ ምርታቸውን በስፋት የሚያስተዋውቁበትንና የሚሸጡበትን አውድ መፍጠርና እድሉን እንዲጠቀሙበት ቅድሚያ መስጠት ተገቢ ነው ብለን እናምናለን፡፡

ድርጅቱ ምርቱን በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ባሉ በታወቁ ላቦራቶሪዎች አስመርምሮ ጥራቱ የተመሰከረለት ለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ለጂኦተርማል ኃይለ ማመንጫ ቁፋሮ፣ለግድብና ለመስኖ ልማት ሥራዎች፣ለውሃ ማቆርና ለተለያዩ የግንባታ ሥራዎችና የኮስሞቲክስ ምርት ግብዓትነት የሚውሉ የቤንቶናይ ምርቶችን አምርቶ ለገበያ ያቀረበ በመሆኑ የዚህ ምርት ተጠቃሚ የሆናችሁ አካላትና ባለሙያዎች ጭምር ተገቢውን ድጋፍ እንድታደርጉላቸው ይህን የድጋፍ ደብዳቤ የሰጠናቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

Ibraahim Dicilu Hakba
ኢብራሂም ዲሂሉ ሃክባ
Ciggiila Biiro Saqala
ምክትል ቢሮ ኃላፊ

<u>ግልባጭ</u>:-

- ለአፋር ቤንቶናይት ሚኒራል ማይኒንግና ፕሮዳክሽን ኃላ/የተ/የማህበር